www.ethiopianorthodox.org

# ወርቃማው ሕግ

ከዲ.ን ማርያም ተስፋዬ (ካለፈው የቀጠለ)

ፍቅር፥ የክርስትና ሃይማኖት መለያ ነው። በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት የሥነ ፍጥረት ገዥ ልዑል እግዚአብሔር ሰውን የሚወድ፣ የሚያፈቅር፣ ስለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ቢመሰክሩም በምሳሌ በመገለጽና በራዕይ ይታይ የነበረው ለጥቂት ወዳጆቹ ነበር። ድምፁን ግን በነቢያት አማካይነት አብዛኛውን ጊዜያት በማሰማት ንስሐ ግቡ የሚል ማስጠንቀቂያ የሚያጽናና መልእክቶችን ያሰማ ነበር።

የሰው ልጆች ከቸር አምላካቸው ተለይተው፣ ብርሃን ለብሰውና ተጎናጽፈው ይኖሩ ከነበሩበት የደስታ ምድር (ገነት) ከተባረሩ በኋላ በአጋንንት አገዛዝ ተይዘው መሰቃየታቸውን የተመለከተው እግዚአብሔር የቀደመ ክብራቸውን ሊመልስላቸው በመውደዱ ከታላቁ መንበሩ ወርዶ ሰው ሆነ።

እንደ ጥንቱ በራዕይ ድምፅ በማሰማት ሳይሆን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖ በሥጋ ተገለጠ፣ ለጥቂቶች ሳይሆን ለአሕዛብ ለበቃ ላልበቃ (ሥጋዌውን) ሰው መሆኑን ለዓለም ገለጠው። በመድኅኔ ዓለም መወለድ በሞት ጥላ በሲዖል ጨለማ ለነበሩት ብርሃን ወጣላቸው የጠላት ዲያብሎስን ምክር በመስማት ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት ተጣልተው የነበሩ ሰውና መላእክት ሕዝብና አሕዛብ፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሰውና እግዚአብሔር ታረቁ ተስማሙ ተፋቀሩ፣ በሌላ በኩል ግን ሰይጣን ያደረባቸው ሄሮድስና ተከታዮቹ በአማኑኤል መወለድ ደነገጡ፤ ምሥጢሩ ግን በየሰው ልቡና ያደጉ አጋንንት መደንገጣቸውን ሥልጣናቸው መሻሩን የሚያበስር ነው። አምላካችን በልደቱ አማካይነት ያጎናጸፈንን ታላቅ ክብር በአንክሮ እናስተውለው፣ ስለኛ ያሳየውንም ፍቅሩን እናድንቅለት።

ከገነት የተሰደድነውን የሰው ልጆችን ወደ ጥንት ርስታችን ሊመልሰን ፈጣሪያችን ስለኛ ብሎ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ወደ ምድረ ግብፅ ተሰደደ፣ ከስደት መልስ በኋላ አማኑኤል ለእናቱ እየታዘዘ በቁመትና በጥበብ አደገ፣ በሠላሳ ዓመቱ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ አርባ መዓልትና ሌሊት ደም ዲያብሎስ ያቀረበለትን ፈተና ከአከሸፈበት በኋላ ሕይወት ሰጪ ትምህርቱን ለተከታዮቹ ማስተላለፍ ጀመረ።

ለይቅርታና ለምሀረት ወደዚህ ዓለም የመጣው እግዚአብሔር ወልድ የእውነትን ፍቅር መገኛ የፍቅር ምንጭ እንደመሆኑ ቀራጮችና ኃጢአተኞችን በፍቅርና በርህራሄ አይን ይመለከታቸው ነበር። ተስፋ የቆረጡትን በማጽናናት ደዌ ሥጋን በተአምራት ደዌ ነፍስን በትምህርት ከመፈወስ ጋር ለእነርሱም ያለውን አምላካዊ ፍቅር በመግለጽ ወደ እርሱ ያቀርባቸው ነበር።

በቀራንዮ አደባባይ እለተ ዓርብ መድኀኔዓለም በስቅለቱ ለዓለም ያለውን ፍቅሩን የገለጸበት ድርጊት ግን ቃላት ሊገልጹት የማይችል እጅግ አስደናቂና ወደር የማይገኝለት ነው። አምላካችን መስቀል ተሸክሞ፥ ከለመዳ ታጥቆ፥ ተሰቅሎ ሁሉ ተፈጸመ፥ በማለት በጽንስ የጀመረውን የቤዛነት ሥራ በስቅለቱ ፈጸመው። የፍቅሩን መጠን በዕለተ ዓርብ በዓይኑ የተመለከተው ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ መላ ዕድሜውን ሲያነባ ኖረ፣ በብቃት በመገለጥና በራዕይ የቀራንዮ መከራ የተገለጸላቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች ዘመናቸውን በሐዘን የወልደ እግዚአብሔርን ስቅለት በማሰብ በዋሻ፣ በጫካ፣ በጸሎትና በጾም በእንባና በሰጊድ አሳለፉት። በአምላካቸው የፍቅር ሰንሰለት ልባቸው ታስሮ ነበርና የፍቅሩ ምርኮኞች ተከታዮቹ ሆኑ፤ በቀራንዮ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን ወልደ እግዚአብሔርን በማሰብ ፈቃደ ሥጋን፣ ፈቃደ ዓለምን፣ ፈቃደ ሰይጣንን ተከራክረው ድል ስለነሱ የክብርን አክሊል ተጎናጸፉ።

ሰማዕታት በመንፈሳዊት ፍቅር ተማርከው ስለ አምላካቸው ስም በዓላውያን ነገሥታት ፊት እየመሰከሩ ወደ እሳት ሲጥሏቸው ሹመትና ሽልማት እንደተሰጠው ሰው ወደር የማይገኝለት ደስታ ይሰማቸው ነበር።

ስለዚህ ነው ብርሃን ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈላቸው ክታቡ «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?» ሮሜ.፰፥፴፭። በማለት የተናገረው። እኛስ አምላካችንን እስከምን ድረስ እንወደዋለን? ይህንን ጽሑፍ ለምታነቡ ክርስቲያኖች የቀረበ ጥያቄ ነው። ለመሆኑ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የምንገኝ የእግዚአብሔር ሰዎች ከዚህ በላይ የተገለጸውን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ጥቅሱን ብቻ ነው የምናውቀው? ወይስ ተግባሩን? ጭንቀት መከራ ሊያጋጥመኝ ይችላል በሚል ግምት ጭንቀት ሳያገኘን አይቀርም በሚል መላምት፣ ስደት ወይም ራብን በመፍራት አምላካችንን ከመካድ እንድን ዘንድ እንጸልይ።

ለታማኙ ሐዋርያ አሸናፊነትን የሰጠው ልዑል እግዚአብሔር እኛንም በሃይማኖታችን ያጽናን። በሃይማኖት ምክንያት የሚደርሰውን መከራ መታገስ እግዚአብሔርን የመውደድ ምልክት ነው። እግዚአብሔርን መውደድ ሕጉን በመጠበቅ ትዕዛዙን በመፈጸም በተግባር የሚረጋገጥ መሆኑን እናስተውል።

(ፍቅረቢጽ፣ ባልንጀራን ስለመውደድ)

ፍቅር የሕግጋት ራዕስ ወይም ጉልላት ነው። ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና። አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደ ነፍስ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቃልሎአል። ሮሜ.13፥9። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው። ፍቅረ እግዚአብሔር በልባችን ካለ፣ መልካም የሆኑትን ምግባራት ለመፈጸም ኃይል እናገኛለን።

መንፈሳዊት ፍቅር ከምግባራት ሁሉ ቅድሚያ ያላት ናት። ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ምጽዋት፣ ወዘተ. ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ መሆናቸው ቢታወቅም ቂምና በቀል ይዘ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የሚፈጸሙት ትሩፋት ግን ቅድመ እግዚአብሔር የማይደርስ መሆኑ ታውቋል። ምክንያቱም ፍቅረቢጽ የምግባራት መሠረት በመሆኗ እሷን ሳይጨብጡ የእግዚአብሔርን ፊት ማየት የማይቻል በመሆኑ ነው። ከፍቅር ጠባዮች አንዱ ይቅርታ ስለሆነ መድኀኔዓለም በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር ስለዚህ ነው እንዲህ በማለት የተናገረው፤ «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀ ድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።» ማቴ.፭፥፳፫—፳፬።

ያለ ፍቅረቢጽ የጸጋ ስጦታዎች ጠቀሜታ የላቸውም። ትንቢት፥ የዓለምን ቋንቋዎች የማወቅ ችሎታ ፍጹም እምነት ያለው ሰው ቢኖር ፍቅረ ቢጹን ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ጋር ካላዋሃደ ሌላውንም ራሱንም ለመጥቀም እንደማይችል ተጽፏል። 1ቆሮ.13፥1—3።

ፍቅር ያስታግሳል፤ መታገስ ማለት ነገር አላፊ፤ ሆደ ሰፊ መሆን ነው። ፍቅር ካለ አንዱ ሌላውን ይታገሳል።

ፍቅር ያስተዛዝናል፤ መተዛዘን ማለት አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ በማለት የሚገኝ ስምምነት ነው። ፍቅር ያለው ሰው በተፈጥሮ የሚመስለው ወንድሙ ወይም የምትመስ ለው እህቱ በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት ሲያገኛቸው መከራ ሲያጋጥማቸው እቅሙ በፈቀደው መጠን በምክር፤ በገንዘብ በጉልበት በሐሳብ ይረዳል። ፍቅሩንም በጐላ፤ በተረዳ ሁኔታ በሚፈጽመው መልካም ምግባር ይገልጻል፥ ያረጋግጣል። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተመዘገበው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ለተፈጠሩ ሰዎች በማዘን የሰው ልጆች አምላካቸውን ከደው ጣዖት በማምለክ እንዳይጎዱ ስለ እውነተኛው የፍጥረት ባለቤት (ገገር) ያስተማሩ፥ ድሀ ተበደለ ፍርድ ጎደለ በማለት ነገሥታትን የገሰጹ፥ የእግዚአብሔር ነቢያት ጻድቃን ሰማዕታት እንደነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል። ከልብ በመነጨ እውነትን የሚፈልግ ሀሳብ በመመራታቸውም የሰው ልጆች የደስታና የሰላም ዘመናትን ለማሳለፍ በቅተዋል።

ፍቅር አያቀናናም፤ ትንአት ማለት በወንድም ላይ ክፉ ማሰብ ማለት ነው፤ ትንአት «ክፉ የሥጋ ፈቃድ ነው» የሚያስተውል ሰው በመጥፎቱ ምክንያት አንዱ በሌላው ላይ ይቀናል እንጂ ዓለም አላፊ፤ መልክ ረጋፊ፤ ገንዘብ ጠፊ የሚቀና በት ሰውና በቅንዓት የሚነዱ ሰዎችም ሟች መሆናቸውን ቢገነዘቡ ፍቅርን መሥርተው መኖር ይችሉ ነበር። ወን ድሙን በቅንዓት ተነሳስቶ ከገደለው ከቃየል ጀምሮ በቅንዓት መንፈስ በመነሳሳት ወንድሞቻቸውን የገደሉ ያሰናከሉ ሥር ምሰው ቅጠል በጥሰው ሰዎችን የጐዱ ቀናተኞች ከጥንት ጀምሮ እስከዓለንበት ዘመን ድረስ እንዳሉ ግልጽ ነው።

በዚህ አጋጣሚ በቅንዓት መንፈስ ተይዘው ሰይጣናዊ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ከስህተታቸው ተመልሰው ንስሐ እንዲገቡ ምክራችንን እንለግሳለን።

ፍቅር አያስመካም፤ ትምክህት ማለት በራስ ሥራ መታመን ራስን ማምለክ ማለት ነው። በመሠረቱ ጥበብ ሥጋዊና፤ ጥበብ መንፈሳዊ የሚገኘው በእግዚአብሔር ቸርነት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። ስለዚህ ሰው አዋቂ ጉልበት ያለው ቢሆን በሕመምና በሌሎች ምክንያቶች እውቀቱ ኃይሉን ሊወስድበት እንደ ሚችል ማመን ይኖርበታል መንፈሳዊ ጸጋም በእግዚአብሔር የተሰጠው ሰው አጋንንትን የማራቅ፤ ትንቢት የመናገር ወዘተ ቢሆን ከጊዜ በኋላ በፈተና ሊጠፉ እንደሚችል ማሰብ ያስፈልጋል። ስለዚህ በተለይ ለክር ስቲያን ከትምክህት መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ማግኘት አለበት። በትምክህት በመነሳሳት ሌሎችን ከማሳዘንና ፍቅር ከማጉደል መጠበቅ በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር በኩል ከማስመስገኑም በተጨማሪ ከትምክህት ራሱን የጠበቀ ሰው አስተዋይ ሊባል ይችላል።

ፍቅር አያስታብይም፤ ትዕቢት ማለት ምንነትን አለማወቅ እንደ እግዚአብሔር አመስግኑኝ ስገዱልኝ ማለት ነው። ፍጹም ፍቅር በልቡ ያደረ ሰው በሌሎች ላይ አይታበይም፤ ከልዑል እግዚአብሔር የተሰ ጠው ሥልጣን፥ ሀብት ወዘተ ቢኖር በአግባቡ ይገለገልበታል እንጂ በሥልጣኑ በመታበይ ግፍን አይፈ ጽምም፤ ገንዘቡን አያመልክም፤ በሀብቱ አይመካም ፈጣሪውን አይክድም።

ፍቅር ብቻዬን ይድላኝ አይልም፤ ለሌላው ያስባል፤ ካለው ያካፍላል፤ እኔን የሚያስፈልገኝ ለወንድሜም

www.ethiopianorthodox.org

ያሻዋል ይላል። በሰዎች መካከል መተሳሰብ ቢኖር ድሆች አይራቡም፤ መጠጊያ አጥተው በረንዳ አያድሩም ነበር። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለራሴ ብቻ ይሙላልኝ ከሚል ራስን የመውደድ ስሜት ርቀን በሌሊት በማ፟ብ ራሳችንን ለርህራሄ ተግባር እንሽቀዳደም። «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ» ተብሎ ተጽፏልና አልጫውን ዓለም በመልካም ሥራችን እና ጣፍጠው።

ፍቅር አያበሳጭም፤ ብስጭት መናደድ ማለት ነው በዚህ ምክንያት ወንድምን ማሳዘን ነው በሰዎች መበሳጨት ከፍቅር ጉድለት የሚከሰት ድርጊት መሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ ብስጭትን አርቀን ፍቅራችን ፍጹም ይሆን ዘንድ እንጸልይ ሰማያዊ አባታችን በኛ ኃጢአት የሚበሳጭ ቢሆን ኖሮ በምድር ላይ ለአንድ ሰዓት ሳይሆን ለአንዲት ሰከንድ መቆየት እንደማንችል እናስተውል፤ እኛም ሌሎችን በመታገስ አምላካችንን ለመምሰል እንሞክር የትእግስት ባለቤት ትእግስትን ያድለን።

ፍቅር ክፉውን ነገር አያስብም፤ ስለዚህ ነው ፍቅር ያለው ሰው ክፉ ነገር አያጋጥመውም የሚባለው። ክፉትን አያስብምና፤ መልካም ዕድል እንዲያጋጥመን ከፈለግን ክፉ ሃሳቦችን እናስወግድ፤ ሌሎችን የሚወድ ሰው በማንም ላይ ክፉትን አያስብም ቢበድሉት በይቅርታ፥ ሊያጠፉት እንኳን ቢያስቡ በሃይማኖት ተቃዋሚዎችን ያሸንፋቸዋል። በፍቅረ ቢጽ ፍጹምነት የነበረው ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለ ፈጣሪው ክብር በመመስከሩ ተቃዋሚ ዎቹ ሲወግሩት መድኀኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ለአይሁድ ከአባቱ ዘንድ ይቅርታን እንደ ለመነላቸው እርሱም ጌታ ኢየሱስ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኾ እንደጸለየ ተጽፏል። የሐዋ.፯፥፷።

ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ በአመፅ አይደሰትም፤ ፍቅር የእውነት መሠረት ከሆነው ከእግ ዚአብሔር የተገኘ በመሆኑ ፍቅር ያለው ሰው እውነተኛና በእውነት ሀሴት የሚያደርግ ነው። ከዓመፅ ሥራ ጋር አይተባበርም።

ክርስቲያኖች ሆይ በፍቅረ እግዚ አብሔርና በፍቅረ ቢጽ ለመኖር እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

የፍቅር አምላክ ፍቅርን እንደሸማ ያላብሰን። አሜን። ✣